# ኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር

ሴፕቴምበር 21 ቀን 2006

ከኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴና የግንባሩ የአለም አቀፍ የውጭ ጉዳይ ኮሚቴ የተሰጠ የአቋም መግለጫ::

የአለም አቀፍ የውጭ ጉዳይ ኮሚቴ ከሴፕቴምበር 9 ቀን 2006 ዓ/ም እስከ ሴፕቴምበር 19 ቀን 2006 ዓ/ም የኢትዮጵያ ህዝብ ዓርበኞች ወደሚገኙበት ግንባር ድረስ በመሄድ ለኢትዮጵያ አንድነትና ነፃነት በመስዋዕትነት በመክፈል ላይ ያሉ ጀግኖች አርበኞቻችንን በአካል በመገናኘት በተለያዩ ሃገራዊና ወቅታዊ የኢትዮጵያ ጉዳዮች ላይ ጥልቀት ያለው የጋራ ውይይት የተደረገ ሲሆን በተጨማሪም የሞራል የገንዘብና የቁሳቁስ ድጋፍ የተከናወነበት ታሪካዊ ወቅት ነበር::

እንዲሁም የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላትና የግንባሩ የውጭ ጉዳይ ኮሚቴ አባላቶች ባደረጉት የ5 ቀናቶች ስብሰባ:-

- ሀ. በስራ አስፈፃሚና በውጭ ጉዳይ ኮሚቴ በኩል የተደረጉ የስራ ክንውኖች ሪፖርትን በማዳመጥ የጋራ ውሳኔ ላይ መድረስ ተችሏል::
- ለ. ግንባሩ አገራችንን ነፃ ለማውጣት በሚያደረገው የትግል ጉዞ የትግል ስልቱንና ለሃገራችን ያለውን ራዕይ በጥልቀት በመመርመር በአንድ ድምፅ ውሳኔ ላይ ደርሷል::
- ሐ. እነኚህን ዝርዝር ጉዳዮች ተግባራዊ ለማድረግ የአጭርና የረዥም ጊዜ እቅዶች በማውጣት አፅድቋል::

ከላይ የተዘረዘሩትን ጉዳዮች የግንባሩ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴና የአለም አቀፍ የውጭ ጉዳይ ኮሚቴው በጥልቀት በመመርመር የአጭርና የረዥም ጊዜ የስራ እቅዶችን በነደፈበትና የተካሄዱ የስራ ክንውኖችን ግምገማ በማድረግ የጋራ ውሳኔዎችን ባፀደቀበት በዚህ ታሪካዊ ወቅት የሃገራችንን ኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታ በማገናዘብ በህዝባችን ላይ የሚደርሰውን ሰቆቃ በመኮነን የሚከተለውን የአቋም መግለጫ አውጥቷል::

1. በተለመደው የወያኔ ፕሮፓጋንዳና የፈጠራ የውሸት ክስ ተከሰው ለወራቶች ያለምንም ፍርድ በወያኔ የማጎሪያ እስር ቤቶች በመጉላላትና በመሰቃየት ላይ ያሉ የኢትዮጵያ ህዝብ የመረጣቸው የህሊና እስረኛ የሆኑት ከፍተኛ የቅንጅት መሪዎች የነፃው ጋዜጣ ባልደረቦች የብዙሃን ማህበራት አባላትና በግፍ የታሰሩ ኢትዮጵያውያን በሙሉ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንደፈቱ::
2. በወያኔ ቁጥጥር ስር ያላችሁ መለዮ ለባሾች ሁሉ በህዝባችን ላይ የሚደርሰውን ሰቆቃ ለማቆም የዜጋና የሃገራዊ ሃላፊነት ስላለባችሁ በቅርቡ ከተራ እስከ ከፍተኛ ማዕረግ ያላቸው የመለዮ ለባሾች የወሰዱትን አቋም ምሳሌነት በመከተል ወያኔን አንበርክኮ ኢትዮጵያን ነፃ በማውጣት ሰላምና ዴሞክራሲ በሃገራችን እንዲሰፍን ለሚከፈለው መስዋእትነት አጋዥ በመሆን ከኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ጎን በጋራ እንድትሰለፉ ጥሪያችንን እናቀርባለን::
3. የህዝባችንን ሰቆቃ ከመጤፍ ባለመቁጠር ሆድ አደሮች የሆናችሁ ሁሉ የወገኖቻችንን ስቃይ እንዲራዘም የወያኔ አጋር መሆናችሁን በማቆም አቋማችሁን በማስተካከል ከህዝብ ጎን እንድትሰለፉ እናሳስባለን::
4. በተለያዩ የትግል ስልቶችና ፕሮግራሞች በግልም ሆነ በቡድን በተቃዋሚ ጎራ የተሰለፋችሁ በሙሉ የዕርስ በዕርስ መጠላለፍን

በማቆምና የግል ፍላጎታችንን በመተው ትኩረታችንን ወያኔ ላይ በማድረግ ሃገራዊ ጉዳዮችን በማስቀደም ሃገራችን ሰላምን ዴሞክራሲ

የሰፈነባት እንድትሆን የተባበረ ትግል እንድናደርግ ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡

5. በሃገር ውስጥም ሆነ በውጭ የምትገኙ መላ ኢትዮጵያኖች በሙሉ የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ኢትዮጵያን ለማዳን በሚደረገው የነፃነት መስዋዕትነት ከጎኑ በመቆም በመፍጨርጨር ላይ ያለወን ዘረኛና ጨካኙን ወያኔ በጋራ እንድናበረክክ ታላቅ ሃገራዊ ጥሪ እናቀርባለን፡፡

## ኢትዮጵያ በቆራጥ ልጆቿ መስዋዕትነት እንድነቷንና ነፃነቷን ጠብቃ ለዘላለም ትኖራለች፡፡

## አንድነት ሃይል ነው፡፡

## የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር!!!